የፌደራል ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ
SSA

ዜና መጽሔት

ጥር 2003 ዓ.ም

በኮሙኒኬሽን
ዳይሬክቶሬት የተዘጋ
ወራዊ ዜና መጽሔት

# ዝቅተኛውን የጡረታ አበል 84 በመቶ ማሳደጉን የፌደራል ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ አስታወቀ

ዝቅተኛ የጡረታ አበል የሚያገኙ የጡረታ ባለመብቶች እየናረ የመጣውን የንሮ ውድነት ለመቋቋም እንዲችሉ መንግስት በዝቅተኛው የጡረታ አበል ላይ 84 በመቶ ጭማሪ አድርጓል ፡፡

የፌደራል ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ዳባ ኦሪያ ጥር 7/2003 ዓ.ም በጽ/ቤታቸው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ የጡረታ አበል ጭማሪ የሚደረገው በጡረታ አዋጁ መሰረት የፈንዱ አቅም እየተጠና በ5 አመት አንድ ጊዜ ነው ፡፡ ይሁን እንጂ መንግስት አሁን ያለውን የኑሮ ውድነት ከግምት በማስገባት እና የጡረተኞች የመግዛት አቅም እንዲጎለብት በአዋጁ የተቀመጠውን ጊዜ ሳይጠብቅ በዝቅተኛው የጡረታ አበል ክፍያ ላይ ከጥር ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ የ84 በመቶ ጭማሪ ማድረጉን ተናግረዋል ፡፡

በአሁኑ ጊዜ 640 ሺ የሚሆኑ የጡረታ ባለመብቶች እንዳሉ የተናገሩት ዳይሬክተሩ ግማሽ የሚሆኑ ባለመብቶች ከሁለት መቶ ብር በታች አበል የሚቀበሉ እንደሆኑ አስረድተዋል ፡፡ ከጥር 2003 ዓ.ም ጀምሮ በሚደረገው ማስተካያ መሰረት ዝቅተኛ የጡረታ አበል ክፍያ የነበረውን 160 ብር በ84 በመቶ በማሳደግ ወደ 294 ብር ከፍ እንዲል መወሰኑን በጋዜጣዊ መግለጫቸው አመልክተዋል ፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ ከሰራተኞች 4 ከመቶ ከአሰሪዎች 6 ከመቶ የነበረው የጡረታ መዋጮ ላለፉት 50 አመታት አልተቀየረም ፡፡ ይሁን እንጂ መንግስት ማህበራዊ ዋስትናን ለማጠናከር በወሰደው እርምጃ እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ከሰራተኞች 7 ከመቶ



በጋዜጣዊ መግለጫ ወቅት




የፌደራል ማ/ዋ/ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር
አቶ ዳባ ኦሪያ

ከአሰሪዎች 11 ከመቶ ለማድረስ መወሰኑን ተናግረዋል ፡፡

በሌላ በኩል መንግስት ያደረገውን የጡረታ አበል ጭማሪ አስመልክቶ አንዳንድ የጡረታ ባለመብቶች ለኤጀንሲው የኮሙኑኬሽን ዳይሬክቶሬት በሰጡት አስተያየት ጭማሪው መንግስት ለጡረተኞች የሰጠውን ልዩ ትኩረት የሚያመለክት በመሆኑ መደሰታቸውን ተናግረዋል ፡፡

የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዘዳንት ሊቀ ትጉሃን አስታጥቄ አባተ በሰጡት አስተያየት ጭማሪው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የብዙ ጡረተኞችን ህይወት የሚያሻሽል እንደሆነ ተናግረዋል ፡፡ መንግስት የሀገር ባለውለታ ለሆኑ ጡረተኞች ሀገሪቱ እያስመዘገበችው ካለችው ልማትና እድገት ተካፋይ ማድረጉና የተከሰተውን ኑሮ ውድነት እንዲቋቋሙ መደገፉ ለጡረተኛ አረጋውያንም ትልቅ ተስፋ ይሆናቸዋል ፡፡ ለወጣቱ ትውልድም እናትና አባቱን በመጦሩ ትልቅ ኩራት ነው ፡፡ መንግስት እየወሰደ ባለው እርምጃ ሊመሰገን ይገባዋል ብለዋል፡፡

የኑሮ ንረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ የሚታወቅ ነው ። ይህ ደግሞ አነስተኛ የጡረታ አበል ተከፋይ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል የመግዛት አቅም እያሳነሰው መጥቷል። ይህንንም በማጤን መንግስት የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል ። ከነዚህ እርምጃዎች አንዱ የጡረታ አበል ጭማሪ ነው ።ሀገሪቱ የነደፈችውን የትራንስፎርሜሽን እና እድገት እቅድን ለመተግበር የያዘችውን አጠቃላይ አቅጣጫዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይፋ ባደረጉበት ወቅት የጡረታ አበል ጭማሪ እንደሚደረግ ተናግረው ነበር ። የፌደራል ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲም የጡረታ አበል ጭማሪ መደረጉን እና ከየካቲት ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ ክፍያ እንደሚፈጸም ይፋ አድርጓል ። በዚህም መሰረት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በጭማሪው ዙሪያ የባለመብቶችን አስተያየት አጠናቅሮ እንደሚከተለው አዘጋጅቶታል ።



"ይህ መንግስት የወሰነው አበል ጭማሪ ጡረተኞች እንዳልተዘነጉ ያረጋገጠ ነው ። ጭማሪው ብዙዎችን ሊደግፍ የሚችል እንደሆነ አምናለሁ ። በጣም ዝቅተኛ አበል የሚከፈላቸው ጡረተኞች ኑሮአቸው እየከበደ እንደነበር እገነዘባለሁ ። መንግስት ባደረገው ጭማሪ እንደሚደገፉ እና የተሻለ እንደሚኖሩ እምነት አለኝ ። ይህም በጣም እንድደሰት አድርጎኛል ። መንግስት ከጭማሪው ሌላ ገበያውን ለመቆጣጠር እና የመግዛት አቅማችን እንዲያድግ የጀመረውን ጥረት መቀጠል አለበት እላለሁ ። ምክንያቱም ምንም ያህል አበል ቢጨመር ገበያው እስካልተረጋጋ ድረስ ጭማሪው ትርጉም አይኖረውም ። ስለሆነም ገበያውን ለማረጋጋት የተጀመረው ጥረት መጠናከር አለበት ።”

የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር ፕሬዝዳንት ኮሎኔል መሰለ ተሰማ



*የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዝዳንት ሊቀ ትጉሀን አስታጥቄ አባተ*

“የተደረገው የጡረታ አበል ጭማሪ ለጡረተኛ አረጋውያንና አርበኞች የኑሮ ውድነቱን እንዲቋቋሙ የሚስችላቸው ነው። መንግስት ኑሯችንን ለማሻሻል

በሚያስችል መልኩ እርምጃ በመውሰዱ የሚበረታታ እና የሚያስደስት ነው ።ሀገሪቷ ካፈራችው ልማትና እድገት ጡረተኞች እንድንጠቀም በመደረጉ ለኛ ትልቅ ተስፋ ለወጣቱ ትውልድም ትልቅ ኩራት ነው ።ሰው

ሰርቶ ሰርቶ አቅሙ ሲደክም መጦሩ ግድ ነው ፡፡ መንግስትና ህዝብም ደግሞ ግዴታውን ወስዶ ለእናትና ለአባት ጡረተኞች ያለውን አክበሮት የገለጸበት በመሆኑ ደስታ እንዲሰማን አድርጓል ፡፡ እርምጃው ለመላው ኢትዮጵያም ዋስትና ለመንግስትም ትልቅ ክብር ነው፡፡”

*የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዝዳንት ሊቀ ትጉሀን አስታጥቄ አባተ ፡፡*



“መንግስት የጡረታ አበል ጭማሪ በማድረጉ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶኛል ፡፡ምክንያቱም ካለው የኑሮ ውድነት አንጻር ብዙዎቻችን ችግር ውስጥ ነበርን ፡፡ ብዙ ቤተሰብ ያለን ኑሮው ይበልጥ አሳሳቢ ሆኖብን ነበር ፡፡ አሁን የተደረገው ጭማሪ ኑሯችንን እደሚያሻሽልን ተስፋ አደርጋለሁ ፡፡”

*የሆለታ ከተማ ጡረተኛ የሆኑት አቶ አሰራት ገ/ሚካኤል*



“ጭማሪው የሚያስደስት ነው ፡፡ እድሜ ከሰጠንም ይህ ትልቅ ጸጋ ነው ፡፡ መንግስት ያደረገው ጭማሪ በተለይ ለእኔ አይነት አቅመ ደካሞች የሚደግፍ ነው ፡፡ እግዚያብሔር ይስጥልን ”

*የሰበታ ከተማ ነዋሪ የሆኑት የጡረታ ባለመብት ወ/ሮ ከድጃ ዱባለ ፡፡*



## የአቃቂ ክፍለ ከተማ ጡረተኛ አቶ ቁንቢ ዳባ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል ፡፡

የጡረታ አበል ጭማሪ መደረጉን ስሰማ በጣም ተደስቻለሁ ፡፡ ፡፡በጡረታ ለምንኖር ይህ ትልቅ ተስፋ ነው ፡፡ ለመንግስታችን እረጅም እድሜ ይስጠው ፡፡



“ጭማሪው ካለው የኑሮ ውድነት ጋር በተያያዘ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ያደረገው ነው ፡፡ ይህ ለሁላችንም ትልቅ ደስታን የፈጠረልን ነው ፡፡ የጡረተኞቻችንን ኑሮ ያሻሽላል ፡፡ ለሁሉም ጡረተኞች አስደሳች እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ጭማሪው ከየካቲት 1/2003 ዓ.ም ጀምሮ ይከፈላል ፡፡ በኛ በኩል ስራችንን በወቅቱ ለማጠናቀቅ ከፍተኛ እርብርብ እየተደረገ ይገኛል ፡፡ እስካሁን የደረስንበት ደረጃም የሚያበረታታ ነው፡፡ በአሁኑ ሰአት ሰራተኞች በከፍተኛ ሞራል እየሰሩ ይገኛሉ ፡፡ ጠዋት በማለዳ መበግባትና ማታ አምሽቶ በመስራት ቅዳሜ እና እሁድን ጨምር ሰራተኞች ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ ፡፡ በስራችን ያሉ የዞን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም በተመሳሳይ እየሰሩ በመሆኑ በወቅቱ ክፍ ያ እንፈጽማለን ፡፡”

***የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የመሀል ኢትዮጵያ ሪጅን ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ደበሌ***

